# የሲፒኢ ማጣራት ምርመራ

# ለበሽተኞች የሚሰጥ መረጃ

**በዚህ ጽሑፍ ለቀረበው መረጃ ላይ ጥያቄ ቢኖራችሁ እናንተን ከሚጠብቁ የህክምና ወይም የነርሶች ኣባል ቡድን ጋር መወያየት በጣም ኣስፈላጊ ነው።**

# ስለ ሲፒኢ ግንዛቤ ምንድነው

የያንዳንዱ እንከን የሌለውና ጤናማ ሰው አንጀት አንታሮባክቴርያሲ የሚባል ባክቴርያ ይኖረዋል። እነዚህ ባክቴርያ አንጀት ውስጥ ይኖራሉ፣ ምንም ጉዳት የላቸውም፣ የበላነውን ምግብም ለመንሸራሸር ይረዱናል። ይህ ሁኔታ ቅኝ አገዛዝ ተብሎ ይጠራል። ሆኖም እነዚህ ባክቴርያ የማይገባ ቦታ ውስጥ የተቀመጡ እንደሆነ ማለትም እንደ ፊኛና የደም ስር ውስጥ፣ የቊስልን መመረዝ መነሻ ሊሆኑ ይችላሉ።

ሲፒኢ (Carbapenemase-Producing Enterobacteriaceae (CPE)) የኢንተርባክቴርያሲ ዘር ናቸው፣ እነዚህ በሽታዎች ካርባፐራምስ ተብለው የሚጠሩት አንቲባዮቲክ ኋይለኛ ለሆኑትን መንድሃኒቶች የመቋቋም ችሎታ ፈጥረዋል። ካርባፐንምስ የአንቲባዮቲክስ ተፈላጊ የሆኑት ክምችት ናቸው፣ ዶክቶሮቹም በሌሎች አንቲባዮቲክስ ለመፈወስ ያቃታቸውን በነዚህ ካርባፐነምስ ለመጠቀም ያስችላቸዋል። በሆስፒታላችን ውስጥ የሲፒኢ በሽታ እንዳይራባ መከላከል አስፈላጊ ነው። ይህ ለመጪው ጊዜ በሽታዎችን ለማከም ለማረጋገጥ ያስችላል።

### ሲፒኢ ካለኝ ህክምና ያስፈልገኛል ዎይ?

አይደል፣ አያስፈልግም። የሲፒኢ ህመም ያላቸውን በሽተኞች መታከም አያስፈልጋቸውም፣ ምክንያቱም እነዚህ ባክቴርያ አንጀት ውስጥ አለምንም ጉዳት ይኖራሉ፣ ምንም ችግር አያመጡም። ሆኖም በሲፒኢ ምክንያት የቊስል መመረዝ ያጋጠማቹሁ እንደሆነ አንቲባዮቲክስ መውሰድ ያስፈልጋል።

# ስለ ሲፒኢ የማጣራት ምርመራ የሚሰጠው መረጃ፡

### በሽተኞቹ ሲፒኢ እንዳይኖራቸው ለምን ምርመራ ይደረግላቸዋል?

የሲፒኢ ምርመራ የትኖቹ በሽተኞች የተለከፉ መሆናቸውን ከታወቀ በኋላ የሲፒኢ መራባትና የቊስልን መመረዝ ለመከላከል ይረዳናል።

በሲፒኢ የተነሳ የቊስል መመረዝ ለማከም በጣም አስቸጋሪ ነው። በሲፒኢ የተለከፈውን ሰው ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም የቊስል መመረዝ ካጋጠመ የህክምና ሰራተኞች ተሎ ብለው የበለጠውን አንቲባዮቲክ (ጸረነፍሳት) ሊሰጡት ይችላሉ።

### ለበሽተኞች የሲፒኢ ምርመራ እንዴት ነው የሚደረግላቸው?

ስኮትላንድ ሆስፒታል ውስጥ ለሚገቡ በሽተኞች መጀመሪያ ሲፒኢ እንዳይኖራቸው ምርመራ ይደረግላቸዋል። በሚከተሉት ምክንያቶች ሲፒኢ እንዳይኖራችሁ ልትጠየቁ ትችላላችሁ፣

- ከስኮትላንድ ውጭ የሆነው ሆስፒታል ውስጥ ተኝታችሁ እንደሆነ (ይህም ለዕረፍት በምትመጡበት ጊዜ የደም ዳያላሲስ የተደረገላችሁ እንደሆነ)
- ወይም ሲፒኢ ካለው ሰው ጋር የኖራችሁ እንደሆነ ወይም
- ሌላጊዜ- ሲፒኢ እንዳላችሁ የተረጋገጠ እንደሆነ

### የሲፒኢ ምርመራ እንዴት ነው የሚደረግልኝ?

ለምርመራ የሚሆን ናሙና (ሳምፐል) የምትፈልጉ ከሆነ የህክምና አባል የሆነው ሰው ቂጣችሁ ውስጥ ጥጥ ያስገባል፣ ወይንም ከሰገራ ለምርመራ ናሙና (ሳምፐል) ሊወስዱ ይችላሉ። ሌሎች

ናምናዎችም (ሳምፐሎች) ሊያስፈልጉ ይችላሉ፡ ለምሳሌ ቊስል ወይም ለሽንት ለሚጠቀሙበት ቀጭን ላስቲክ ያስፈልጋል።

እነዚህ ናምናዎች (ሳምፐሎች) በሚወሰዱበት ጊዜ ምን ጊዜም በኣክብሮትና ለብቻዎ ይሆናል።

የምርመራው ጥጥና ናምናዎች (ሳምፐሎች) የትኛው ባክቴርያ እንዳለበት ወደ ላቦራቶሪ ይላካል እና የናንተው የህክምና ቡድን ውጤቱን ይነግሩዋችኋል።

የምርመራውን ውጤት እስኪታወቅ ድረስ ለብቻዎ በኣንድ ክፍል ውስጥ እንዲተኙ ሊጠየቁ ይችላሉ።

## ሲፒኢ ምርመራ ተደርጎላቸው ውጤቱ በሽታው ኣዎንታዊ (ፖሲቲቭ) ከሆነ ለበሽተኞቹ የሚሰጠው መረጃ

### የሲፒኢ ምርመራ ውጤቱ በሽታው ኣዎንታዊ (ፖሲቲቭ) ካመለከተ ምን እሆናለሁ?

የሲፒኢ ምርመራው ተደርጎላችሁ ፖሲቲቭ ከሆነ የሲፒኢ ባክተሪያ ኣላችሁ ማለት ነው። ይህ ሁኔታ ኣብዛኛውን ጊዜ ምንም ችግር ኣያመጣም በተለይም ጤናማ ለሆኑት ሰዎች፡ ምንም የሚያስከትለው ነገር የለም። የቊስሉ ማመርቀዝ ምልክት  ካልተያባችሁ ምንም ህክምና ኣያስፈልገውም።

በበሽታው የተለከፉችሁ እንደሆነ የናንተው ዶክተር የሲፒኢ ባክተሪያ ተሸካሚ መሆናችሁን ማወቁ በጣም ኣስፈላጊ ነው። ይህ ማለት ደግሞ በሽታችሁን ተሎ ለማከም የበለጠውን ኣንቲባዮቲክ (ጸረነፍሳት) ለመምረጥ ያስችላቸዋል።

የሲፒኢ ምርመራችሁ ውጤት ኣዎንታዊ (ፖሲቲቭ) በሽታው መኖሩን ካመለከተ፡ ሆስፒታል ውስጥ እስካላችሁ ድረስ በየሳምንቱ ምርመራ ሊደረግላችሁ ይችላል።

### ሆስፒታል ውስጥ ስቀመጥ የበሽታውን ማመርቀዝ ለመቆጣጠር ምን ይደረጋል?

ሆስፒታል ውስጥ በምትተኙበት ጊዜ ኣንድ ኣልጋ ብቻ ያለበት ክፍል ውስጥ እንድትተኙ ይደረጋል፡ ወይንም የናንተው ዶክተር የሲፒኢ በሽታውን ወደ ሌሎች በሽተኞች እንደማይተላለፉ ካረጋገጠ በኋላ ሊሆን ይችላል።

የበሽታው ማመርቀዝ ለመከላከል የሚደረገው ጥረት፡  ሽንት ቤት ከሄዳችሁ በኋላ በውሃና ሳሙና እጃችሁን በደንብ ማጠብ በጣም ኣስፈላጊ ነው። በተጨማሪ ኣልኮል ያለበት የእጅ ፎጣ መጠቀም ይቻላል። ሌላ ኣስፈላጊ ነገር ደግም የህክምና ነገሮች እንደ የሽንት ላስቲክና (urinary catheters or intravenous drips) በእጃችሁ መያዝ ጥሩ ኣይደለም። ይህ በሲፒኢ ለሚመጣው በሽታ ለመከላከል ይጠቅማችኋል።

### ሰዎች እኔን ለመጎብኘት/ለመጠየቅ ሊመጡ ይችላሉ ዎይ?

ሲፒኢ ተሸካሚ በሽተኞች፡ ሆስፒታል ውስጥ ተኝተው ጠያቂዎች ሊመጡ ይችላሉ። ደካማ የሆኑትን ጠያቂዎች፡ ልጆችና ህጻናቶች፡ ሆስፒታል ውስጥ መጥተው እንዲጠይቋችሁ ምክር ኣይሰጥም። እናንተን ለመጠይቅ ለመጡት ሁሉ ሲገቡና ሲወጡ እጃቸውን መታጠብ ይኖርባቸዋል።

## ከሆስፒታል ከወጣሁ በኋላ ምን እሆናለሁ?

ከሆስፒታል በምትወጡበት ጊዜ ሲፒኢ ተሸካሚ ከሆናችሁ፡ ከጊዜ በኋላ ሊጠፉ ይችላል። እቤታችሁ ስትደርሱ ምንም የምትወስዱት ጥንቃቄ ኣይኖርም ነገር ግን በተለይ ሽንት ቤት ከሄዳችሁ በኋላ እጃችሁን በውኃና ሳሙና፡ በደንብ ማጠብ ይኖርባችኋል። የናንተው ዘመድ ወይ ጓደኛ እቤታችሁ የሚያግዛችሁ ከሆነ፡ እናንተን ከማከም በፊትና ከማከሙ በኋላ እጁን በውሃና ሳሙና በደንብ ማጠብ ይኖርበታል። የኣልጋ ምንጣፍ ልብሶችና ሌላ ጨርቃ ጨርቆች እንደ ድሮው ሊታጠቡ ይችላሉ።

እንደገና ወደ ሆስፒታል ወይም ሌላ የጤና ኣካባቢ በምትሄዱበት ጊዜ እናንተን የሚያክሙት ሰዎች ባለፈው ምርመራ የሲፒኢ በሽታ ፖሲቲቭ እንደነበራችሁ ማሳወቅ በጣም ኣስፈላጊ ነው። ይህ የሲፒኢ በሽታ እንዳይተላለፉ ለማድረግ ይጠቅማል፡ እንዲሁም የሲፒኢ በሽታ እንደገና እንዳያጠቃችሁ ለመከላከል ይጠቅማል።

## ተጨማሪ መረጃ ከየት ኣገኛለሁ?

ተጨማሪ መረጃ ከፈለጋችሁ እናንተን የሚያክሙት የነርሶች ኣባል ለሆኑት ወይም የህክምና ቡድን ኣነጋግሩዋቸው፡ እነሱም በናንተ ምትክ ሆነው ለኣከባቢው የበሽታ መቆጣጠሪያ ቡድን ደውለው ሊያነጋግሩዋቸው ይችላሉ።

**እናንተን ለሚጠቡቁት የህክምና ቡድን ማንኛውም ጥያቄ ቢኖራችሁ በስር ካለው ቦታ ላይ ጻፉላቸው።**

**ይህ ጽሁፍ በሌሎች ቋንቋዎችም ይገኛል በተጨማሪም በትልልቅ ፊደሎች የተጻፈ ይኖራል፣ በቀላሉ ሊነበብም ይችላል፣ በብረይልም ኣለ (ይህ ብረይል በእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቻ ነው)**

**የዚህ ጽሁፍ ግልባጭ ለመጠየቅ ማለትም በሌላ ቋንቋ ወይንም ሌላ ኣቀራረብ የተጻፈ በሄልዝ ፕሮተክሽን ስኮትላንድ** (Health Protection Scotland:) **ብላችሁ በሚቀጥሉት ኢመይል ኣድራሻና ስልክ ቊጥር መደወል ትችላላችሁ፣**

NSS.HPSHAIScreening@nhs.net

Health Protection Scotland
Meridian Court, 5 Cadogan Street, Glasgow G2 6QE
0141 300 1100